# የዘር ፖለቲካ ነጋዴዎች

(ወንድወሰን ተክሉ -ኢትዮሚዲያ አምደኛ)

**መነሻ አንኳር-



*1ኛ-የአማራ ክልላዊ መአተዳድር ምክር ቤትና የመስተዳድሩ ቃል-አቃባይ «በወልዲያ ግጭት የህግ የበላይነት ፈርሶና ስርዓት አልበኝነት ነግሶ ዜጎች በአመለካከታቸውና በማንነታቸው መሰረት ሲጠቁ በሚያሳፍር ሁኔታ ታይቷል፤ …እርምጃውን በወሰዱና ባስተባበሩት ላይ እርምጃ እየተወሰደ ሲሆን የጥቃቱ ኢላማ የሆኑትንም መልሶ ለማቋቋም የክልሉ መስተዳድር ጠንክሮ ይሰራል» በማለት ከሁለት አቅጣጫ ተከታታይ መግለጫ አውጥቷል፡፡

2ኛ-ከህወሃታዊያን መንደር ደግሞ የሆርን አፌርስ ድረ-ገጽ ባለቤትና በርቲክሉ 30'000ክፍያ ከህወሃት እንደሚከፈለው ይፋ የሆነው ዳንኤል ብርሃኔ «የህወሃት አባል ያልሆነ ትግራዋይ አይነካ የሚለውን የእነሱን ክርክር ሳይሆን የምፈልገው የህወሃት አባል ሆነ አልሆነ ትግራዋይ የሆነ ሁሉ መነካት የለበትም ነው የምለው» ሲል ከአይጋ ፎረም የህወሃት ድረ-ገጽ «የትግራይ ህዝብ በማንነቱ ላይ ያነጣጠረ ጄኖሳይድ ጥቃት በጋዛ ወንድሞቹና እህቶቹ ኢላማ ተደርጎ መጠቃትን ከማየት የበለጠ በኢትጵያ እጅግ የሚያሳዝን ነገር የለም…» ሲል የትግራይ ህዝብ ከጨፍጫፊው የደርግ ኮምኒስት ጋር ታግሎ እራሱንና ኢትዮጵያን ነጻ ላወጣ ይህ ጥቃት አይገባውም ሲል ያትታል፡፡

3ኛ-ከተቃዋሚው ጎራ አግ7 እና ደምህት በጋራ ባወጡት መግለጫ «ካለፉት ሶስት ዓመታት ወዲህ በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች በተነሱ የፀረ ወያኔ እንቅስቃሴዎች የበቀል እርምጃ እየተወሰደባቸው ካሉ የህወሃት ካድሬዎች በተጨማሪ ከህወሃት ጋር ምንም አይነት ግንኙነት ያልነበራቸው ሰዎችም የጥቃቱ ሰለባ እንደሆኑ መስማት እየተለመደ መጥቷል፡፡የዚህ ዓይነት ጥቃት እንዳይደርስ መከላከል የሚኖርብን ኢፍትሃዊ ስለሆነ ብቻ ሳይሆን ለዘላቂ ሰላማችንና አንድነታችን አደጋ ስላለው ጭምር ነው፡…ለወገን የሚቆረቆ ቅን ዜጋ ሁሉ ይህን አደገኛ ሁኔታን የማስቆም ግዴታ ይኖርበታል» ሲል በአባላቱና ደጋፊዎቹም ዘንድ ታላቅ ቅዋሜን ያዥጎደጎደለትን መግለጫ አውጥቷል፡፡

4ኛ-ዘረኝነት በራስ ወገን ላይ ብቻ ሲደርስ ማውገዝ ብቻ ሳይሆን በማንኛውም የሰው ልጅ ላይ በማንነቱ ጥቃት ሲደርስበት ማውገዝ ተገቢ ነውና በማንነት ላይ ያነጣጠረ ጥቃትን እናወግዛለን ያሉ አስተያየቶችን ያነበብነውን ያህል ማነው በማን ላይ ማንነት ላይ ተመርኩዞ ጥቃት የፈፀመው በማለት ጉዳዩን በመጠይቅ ሲያዩም ተስተውለዋል፡፡

****

**በዚህ ጽሁፍ -

1ኛ-ዘር ተኮር ጥቃትና የሰሜን ወሎ እውነታ

2ኛ-የብሄር ተኮር ጥቃት(ጄኖሳይድ)ጩህት፤ህወሃትና የትግራይ ህዝብ እውነታዎች -

3ኛ-የጄኖሳይድ ምስጢራዊ ጥቅም ለህወሃት - የሚሉት ነጥቦች ተነስተው መልስ ተሰጥቷቸዋል

***

የሰሜን ወሎዋ ወልዲያና ተጎራባቾቿ ቆቦና መርሳ ሰሞኑን በወታደራዊ ሰራዊት ብቻ ሳይሆን የተወረሩት በፖለቲካ ፕሮፖጋንዳም የተወረሩ ሆነው ታይተዋል፡፡

ለመሆኑ በኢትዮጵያ ውስጥ፤በተለይም በሰሜን ወሎ የተፈጠረው ግጭት በማንነት ላይ ያተኮረ ነውን? ወይንስ የጥር 12ቱ የአግዓዚው ጥቃት ከተሚውን አንቀሳቅሶ በአንድ ነገድ ላይ ያነጣጠረ የብቀላ ጥቃት አስፈፅሟልን?

ማንነትን መሰረት ያደረገ ጥቃት ስንል ምን ማለታችን ነው? የትኛው ወገን ማንኛውን ወገን በማንነቱ ምክንያት ብቻ እየነጠለና እየለየ አጠቃ?

ከሁለት ደርዘን በላይ ዓመታትም በሃላ ዛሬም ሰዎች፤በተለይም ፖለቲከኞች በማንነት ተኮር ጥቃት ነግደው ለማትረፍ ሲሽቀዳደሙ ማየትም ሆነ መስማት እጅግ ቢያሳፍርም፤በይበልጥ ግን እጅግ ያሳዝናል፤ተስፋ አስቆራጭ ስሜትንም ሊያላብስ እጅግ ይታገላል፡፡

እንድ ሀገር በእርግጥም በከፍተኛ ችግር ላይ ያለን ብቻ ሳይሆን ከችግሮቻችን መፍትሄም እጅግ የራቅን መሆናችንን የሚያሳይ እድምታ በመሆኑ ተስፋ ለማስቀረጥ ሲጥር ማየቱ የሚያስደንቅ አይደለም፡፡

የመፍትሄዎች ሁሉ መጀመሪያ የተዘፈቅንበትን ችግርና የያዘንን ህመም አምኖ በመቀበል የሚጀምር ሲሆን ህመሙንና ችግሩን የደበቀ መድሃኒቱንም የተነጠቀ የሚያስብል በመሆኑ እዚህ ላይ ፖለቲከኞቻችን ብቻ ሳይሆኑ ህዝባችንም፤በተለይም በማንነቱ ጥቃት እየተፈጸመበት ነው የተባለው ህዝብ ዘንድ እውነታውን ማጣት መቻል የሁኔታውን እጅግ አሳሳቢነትን የሚያሳይ ሆኖ እናያወለን፡፡

***

**ዘር ተኮር ጥቃትና የሰሜን ወሎ እውነታ፤

ከሁሉ በፊት ፀሓፊው በሰው ልጅ እኩልነት፣በህግ የበላይነት፣በአንዲት ሉዓላዊ ኢትዮጵያዊ አንድነት እና ብሎም በእምነት ነጻነትና በሰው ልጆች ተፈጥሮአዊ መብት ሙሉ በሙሉ መከበር የማያምንና እነዚህም እሴቶች በሀገራችን መሰረት ያላቸው ማህበራዊ መተዳደሪያዎች ይሆኑ ዘንድ እጅግ የሚሻና የተቻለውንም በማድረግ የሚተጋ መሆኑን በመግለፅ የወልዲያውን ግጭት ይዘትና እውነታን ለማስፈር ይወዳል፡፡

በኢትዮጵያ ውስጥ ብሄር ተኮር ግጭት እየተፈፀመ አይደለም በሚል አቋም የምንገታገት የቀን ህልመኛ አይደለሁም፡፡ በህወሃት ፍቃድና ፍላጎት የትግራይ ህዝብ በተለየ ሁኔታ በተቀረው ኢትዮጵያዊ ወገኑ ተለይቶ እንዲታይና ብሎም እንዲገለል ያልተደረገ ነው የምልም ሳይሆን ሰሞኑን በመንግስታዊ አካላትና ከተቃዋሚውም ጎራ በሰሜን ወሎ በትግራይ ህዝብ ላይ ነጥሎ በተለየ ሁኔታ የተፈፀመ ጥቃት የለም ወይም ከቶም አልተፈፀመም ስል ከታች ያቀረብኳቸውን እውነታዎችን በማስረጃነት በማቅረብ ነው፡፡

ብሄር ተኮር ጥቃት ስንል ምን ማለታችን ነው? ለምንስ ሰሜን ወሎ በተለየ ሁኔታ የብሄር ተኮር ጥቃት አውድማ ተደርጋ ተመረጠች? በሰሜን ወሎ የተስተዋለው የንብረት ውድመትና ግጭት በሀገሪቱ ውስጥ በእሬቻው ጭፍጨፋ ማግስት በሰበታና መላ ኦሮሚያ ከተከሰተው ከፍተኛ የንብረት ማውደም፤በምስራቅ ኦሮሚያ ለአንድ ሚሊዮን ህዝብ መፈናቀል ምክንያት ከሆነው ጦርነትስ በምን ይለያል? የሰሜን ወሎው የህወሃት ነክ እና መንግስታዊ የሆነን ተቋማትን ማውደም በጎንደር፣ጎጃም፣ኦሮሚያና አዲስ አበባ ላይ ከተፈፀሙት ተመሳሳይ ውድመቶች የተለየ ያደረጋት ምንድነው?

ላለፉት ሶስት ዓመታት በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍል ውስጥ ንብረትነቱ የህወሃት፣የመንግስትና የህወሃት ደጋፊ የሆኑ ንብረቶችና ባለንብረቶቹም የአማራ፣የኦሮሞና የትግራይ ተወላጅ የሆኑት ወድመዋል፤ዛሬም እየወደመ ሳለ የሰሜን ወልዲያ ክስተት የተለየ ያደረገውን ሁኔታ እንዴት ሊታያቸው እንደቻለ አይተን ፈርጀናል የሚሉት ብቻ የሚያውቁት ይሆናል፡፡

ብሄር ተኮር ጥቃት አንድን ለጥቃት የተመረጠን ነገድ የጥቃቱ እርምጃ በተፈፀመበት ስፍራ ያለን በሙሉ የሚያጠቃ እንጂ በማንነቱ ለጥቃት የተመረጠውን ነገድ እየመረጡና እየለዩ የሚፈፅሙት ጥቃት አይደለም፡፡

በሰሜን ወሎ ሶስት ከተሞች ለጥቃት የተመረጠው የትግራይ ነገድ ነው ብለን ከተስማማን የጥቃቱ ሰለባ የሆነው ግን ንብረትነቱ መንግስታዊ፣ድርጅታዊና የግለሰቦች ደግሞ እንደ ግለአቋማቸውና አመለካከታቸው የአማራውና የትግራይ ተወላጅ የሆኑ ንብረቶች እንደወደመ እንረዳለን፡፡

እንደ የአማራው ክልል መስተዳድር ምክር ቤት መግለጫ በሶስቱ ከተሞች የ15 ሰዎች ህይወት መጥፋቱ የተገለጸ ሲሆን ከእነዚህም ውስጥ የሁለቱ ማንነት ከፀጥታ አስከባሪው ሃይል ነው ይልና የ13ቱን ማንነት የአከባቢው ተወላጆች አማሮች መሆናቸውን ይገልጻል፡፡

ከ30በላይ ንጹሃን ህይወት እንደጠፋበት የሚገልጹትን የገለልተኛ ወገኖችን ሪፖርት ወደ ጎን አድርገን የራሱን የመንግስትን ሪፖርት እንደተዓማኒነት ብንወስድ አንድም የትግራይ ተወላጅ በትግሬነቱ ከማቾቹ የአማራ ተወላጆች ጋር ተዳብሎ እንዳልተገደለ በግልጽ እያየን ሳለ በምን ዓይነት ስሌትና ቀመር ሆኖ ነው በዚህ ፍርደኛ በሆነው ህዝብ ላይ ነገድ ተኮር ጥቃት ፈጽሟል ተብሎ የመግለጫና የውግዘት ጋጋታን ሊያኸጎደጉድ የቻለው?

በሶስቱ ከተሞች ውስጥ ከሚኖሩት ከሶስት ሺህ በላይ የትግራይ ተወላጆች አንድም ነፍስ ሳትጠፋ ዘር ተኮር ጥቃትና በትግራይ ህዝብ ላይ የጄኖሳይድ እርምጃ ተወሰደ ተብሎ መለፈፍ በእርግጥ እውነታውን ሳያዩ ቀርተው ነው ወይንስ የተለየና የተደበቀ ፍላጎትና ዓላማ እያራመዱ ነው ያስብላል፡፡

እሳት በሌለበት ጭስ አይታይም እንደሚባለው ለብሄር ተኮር ጄኖሳይድ ፕሮፖጋንዳ እርሾ የሆነው ክስተት በሶስቱ ከተሞች የተፈፀመውን የንብረት ማውደም እርምጃ ውስጥ ንብረትነታቸው የትግራይ ተወላጆች የሆኑ ንብረቶች ስለወደመ እንደሆነ እንረዳለን፡፡

ይህንን እርምጃ በራሱ ስንመረምረው
1ኛ- የወደመው ንብረት ሁሉ የትግራይ ተወላጆች ብቻ አለመሆኑን እናያለን፤
2ኛ-አጠቃላይ የትግራይ ተወላጆች ንብረት የሆነ ሁሉ እንዳልወደመ እናያለን (እንግዲህ ከሶስት ሺህ በላይ ለሆነው በአከባቢው የትግራይ ተወላጆች ንብረት የወደመው በአስሮች የሚቆጠረው ንብረት ብቻ ነው ያላቸው ካልተባልን በስተቀር)

ለመሆኑ ዘር ተኮር ጥቃት ከዚያው ለጥቃት ከተመረጠው ነገድ እየለየና እየመረጠ የሚፈፀም ጥቃት ነውን?

የአማራ ክልል መስተዳድር ብቻ ሳይሆን የትግራይ ክልል መስተዳድርና የህወሃት ካድሬዎችም ጭምር ከተጠቀሙበት እጅግ ወርቃማ ቃላት ውስጥ አንዱ «የህግ የበላይነትን አፍርሰው…» የሚል ይገኝበታል፡፡

ድንቅ ነው ቃሉን በመጠቀማቸው፡፡ ግን ማንኛው ነው የህግ የበላይነትን ያፈረሰው?

ለመሆኑ የወልዲያና ተጎራባቾቹ ሁለቱ ከተሞች ህዝብ እንዲሁ የመዝረፍና የማውደም ሱስ እንደተጠናወተው ሁከተኛና ዘራፊ ህዝብ ብድግ ብሎ ነው እንዴ ያወደማቸውንም ሆነ ዘረፉቸው የተባሉትን እርምጃዎችን የወሰደው?

ለመሆኑ ከ2016ቱ የቢሾፍቱው እሬቻ እልቂት ማግስት በመላ ኦሮሚያ የተከሰተው ነገር ምን ነበር?
በሁለትና ሶስት ጀምበር እድሜ ውስጥ በሰበታ፣በዝዋይ፣በአዋሽና ወዘተ ኦሮሚያ ዞኖች የወደሙት ግዙፍ ግዙፍ ኢንደስትሪ ባለቤቶች ጥቃቱ በማንነታችን ላይ ያነጣጠረ ነው ለምን አላሉም? አብዛኞቹ ንብረቶች የውጭ ዜጎች ስለሆኑ ነው?

የኢሬቻው ጭፍጨፋ በማግስቱ ያንን ሁሉ የአጸፋ መልስ ከህዝቡ ካመጣና ብሎም ስርዓቱ የአስቸካይ ግዜ አዋጅ ለማወጅ የተገደደ ከሆነ በወልዲያ ጥር 12ቀን የተፈጸመው የአግዓዚው ጭፍጨፋ በቀጣዩቹ ቀናት ውስጥ ከህዝቡ የአፀፋ እርምጃ አሰጠ የማንልበት ምክንያት ድርጊቱ በወልዲያ ስለሆነ ነውን?

የህግ የበላይነት እያሉ ዛሬ ከአራቱም ማእዘን የሚያላዝኑ የዘመናችን ፈርኦኖች ያን የበላይነቱን የሚሰብኩለትን ህግ በቅዱስ ታቦቱ ፊት ንፁሃንን ተኩሶ በመግደል ፍርስርሱን እንዳወጡት አላወቁም ማለት ነው? ወይንስ ህጉ የሚሰራው ለአንድ ወገን ብቻ ነው?

አግዓዚው ለዓይኑ ያስጠላውን ለመግደል ህግ ተብዬው ካላገደውና የማች ወገንና ዘመድ የአፀፋ እርምጃ ሲወስድ ህግ አፍርሷል የምንል ከሆነ በእውነት ለመናገር የዚህችን ሀገር ችግር ለመፍታት እየጣርን ሳይሆን መፍትሄ እንዳይገኝለት እየቀበርንና እያወሳሰብን እንዳለን ብንወሻም ልንክደው የማይቻለን ሀቅ እንደሆነ ለመግለጽ እወዳለሁ፡፡

በየትኛውም የዓለም ክፍል ፀድቆ የህዝብና የሀገራት መተዳደሪያ የሆነው ዘርፈ ብዙው ህግ ለሚዳኛው ማንኛውም ዓይነት ክስተት የድርጊቱን መነሻ መንስኤ ምንድነው ሲል ለይቶ በማውጣት ፍርድ ይሰጣል እንጂ ቀድሞ ለከሰሰና ላመለከተ ሁሉ ፍርድ የሚሰጥ የሚሰጥ ቢሆን ኖሮ ምድራችን በስርዓተ አልበኝት የተሞላች በሆነች ነበር፡፡

እንደ ብፁእ አቡነ ኤርሚያስ የሰሜን ወሎ ሀገረ ስብከትና የአቡነ ቄርሎስ ምክትል አገላለጽ የጥምቀት ክብረ በዓል ከመድረሱ ቀደም ብለው ለዞኑ የብአዴን ተጠሪ የመከላከያ ሰራዊቱ እንዳይመጣብን ክብረ በዓሉን በራሳችን ማክበር ስለሚቻለን ሰራዊቱ እንዳይመጣ ብለው አግደውና ስምምነትም ተደርጎ ሳለ ለምንድነው ሳይጠራ፤ብሎም ከስምምነቱ ውጪ ሰራዊቱ ወልዲያ እንዲገኝ የተደረገው?

ያለፈቃድና ያለግብዣ በወልዲያ እንዲገኝ ከተደረገም በሃላ በታሪካችን ታይቶና ተሰምቶ በማይታወቅ ሁኔታ ማን አዞት ነው ጽላቱ ባለበት ንጹሃንን በጥይት የቆላው?

የ13ዓመቱ እምቦቆቅላ ዩሴፍ እሸቱ በእርግጥ ለሰራዊቱና ለጽላቱ አስጊ ሆኖ ነው እንዲገደል የተደረገው?  ወይንስ በጥመቀተ ባህሩና ግርግሩ ባለበት ስፍራ ያልነበረውና በሰላማዊው የከተማ ክፍል የነበረው የ36ዓመቱ ገብረሚካኤል በ5ጥይት ተደብድቦ ለመገደል ያበቃው የትኛው ወንጀሉ ነው?

ጽላቱን ለመንጠቅ ሞከረ? ህዝቡን አስተባበረ?

ለመሆኑ የኢትዮጵያ ህዝብ ለእምነቱ ያለው ቀናኢነትና ታላቅ አክብሮት ይህን በዓመት አንድ ግዜ የሚወጣን የጥምቀት በዓል በገዳይ ጥይትና በጢስ ቦምብ አተራምሰህ የገደልከውን ገድለህ ያሰርከውን ካሰርክ በሃላ «አበጀህ የእኔ ጀግና » ብሎ እንዲገዛልህ ነበር የጠበከው?

በወልዲያ የህግ የበላይነት ፈርሳል የሚለው የባለስልጣቱ ቱልቱላ ቀረርቶ አዎን ድብን ብሎ ተንኮታኩቶ ፈርሳል- ያፈራረሰውም የአንተው አግዓዚ ሰራዊትና ካድሬ ነው የሚል ግልጽና የማያሻማ እውነትን መግለፅና ማሳየት ሲቻል እጥፍ ብሎ በማንነት ላይ ያነጣጠረ ጥቃት ተፈፅማል እያሉ መደስኮር በጽላቱ ፊት ተኩሰህ እንደገደልከው ሁሉ ያሻህን ለግዜው ትንጋራለህ እንጂ ቃልህና ድርጊቱ ሃራምባና ቆቦ ያህል እንደተለያዩ ልገልፅልህ እወዳለሁ፡፡

***

***የብሄር ተኮር ጥቃት(ጄኖሳይድ)ጩህት፤ህወሃትና የትግራይ ህዝብ እውነታዎች -

ሀገራችን በዘር ተኮር ጥቃት ክፉኛ ከተመታች ዓስርተ ዓመታት አስቆጥራለች፡፡ በኢትዮጵያ ውስጥ ዛሬም ሆነ ትናንት ነገድ ተኮር ጥቃቶች የሚፈፅሙት ስልጣን ላይ ባለው ስር ዓትእንጂ ስልጣን አልባ በሆነው፤ ያውም የስርዓቱ ተቃዋሚ ተብሎ በተፈረጀው ነገድና ወገን አይደለም፡፡

ነገር ግን ህወሃት የዘር ተኮር ጥቃት በህዝቤ ላይ ይፈፀማል ወይም ተፈጽሟል ሲል ይህ የመጀመሪያው አይደለም፡፡

ጄኖሳይድ (Interhamway ) የሚለው የሩዋንዳውን የዘር ፍጅት ክስተትን ህወሃት በሀገራችን ያውም በትግራይ ህዝብ ላይ ተፈጽሟል ወይም ሊፈጸም ነው ብሎ መናገር የጀመረው በ1997ቱ ምርጫ ወቅት ቢሆንም ድርጅቱ ግን ቀደም ብሎም የትግራይን ህዝብ እያስፈራራ ያስርበት እንደነበረ በግልፅ ይታወቃል፡፡

በታሪካችን እንደ ህወሃት የጄኖሳይድን ቃል አፍቃሪ መንግስት አይተንም ሆነ ሰምተን አናውቅም፡፡ ከታሪኩ እንደምንረዳው ድርጅቱ ወደ ስልጣን ለመምጣት ሲል በራሱ ወገኖች ላይ በተምቤን እና በሀውዜን አሰቃቂ የህዝብ ፍጅትን በማቀነባበር እንዳስፈጸመ ሁሉ ዛሬም ቢሆን ይህው ድርጅት የትግራይን ህዝብ ከተቀረው ኢትዮጵያዊ ወገኑ በማጋጨትና በጄኖሳይድ ይፈፀምብሃል ማስፈራሪያ ጠፍንጎ በማሰር የስልጣኑ ጠባቂና ተከላካይ አድርጎት መኖርን የሚሻ ድርጅት ነው፡፡

ህወሃትና ጄኖሳይድ እጅግ ይወዳደሉ፡፡ በትግራይ ህዝብ ዘንድ ይበልጥ ተአማኒነት ለማግኘትም ድርጅቱ የነደፈው እስትራቴጂ ትግራይን ከተቀረው ህዝብ ጋር የሚለያይና ጥርስ የሚያናክስ አካሄዶችን በመጠቀም ህዝቡን ነጥሎ መቆጣጠር በሚል አካሄድ ነው፡፡

የጄኖሳይድ ፕሮፖጋንዳውን ተቀባይነትን ለማስረጽ ድርጅቱ እንደዛሬው የወልዲያ አይነቱ ክስተት ሳይፈጠር እንኳን በ1997ቱ ምርጫ ወቅት በአዲስ አበባ ያሉ አጠቃላይ የትግራይ ተወላጆችን ማታ ማታ በየቀበሌው አዳራሽ በሚስጥር እየሰበሰበ «አማራው ንብረት ወደ ቀበሌ ትግሬ ወደ መቀሌ» እያለህ ነው በሚል በማቹ መለስ የተዘጋጀ ትምህርት ከመሬት ተነስቶ በፈጠራ ሲያስተምር መቆየቱን እናውቃለን፡፡

የዛሬውን የወልዲያ ክስተት ኢ-ምንት የማታክል ክስተት በሌለበትና ባልታየበት ሰላማዊ ወረዳ ላይ ህወሃት የትግራይ ተወላጆች እየሰበሰበ «አማራ ሊያጠፋህ ነው፤ ሞት ፈርዶብሃል» እያለ በግድ የጄኖሳይድን ድግስ ከጋተ ዛሬ ላይ በሀገር አቀፍ ደረጃ በየስፍራው የህወሃት ንብረቶች እየተነጠሉ በሚመቱበት ወቅትና ሂደት የሚናፍቀውን ፀረ ትግራይ ጄኖሳይድ ሳይታሰብም ታስቦ ተፈጽሟል ለማለት የሚያበቃውን ግብዓት በገፍ እንዳገኘ ይታየናል እንጂ በእርግጥ የወልዲያ ህዝብ እየተነገረን እንዳለው ጄኖሳይድ የፈፀመ ሆኖ አይደለም ያዙኝ ልቀቁኝን እየሰማን ነው ያለነው፡፡

ማንም ሊክደው የማይቻለው የዘር ተኮር ጥቃት በተለይም ህወሃት እጅግ ተፈጽሞ ለማየት የሚቃትትለትን ጄኖሳይድ እርምጃ በሀገራችን አይፈፀምም ብዬ ልግደረደር ከቶም አይቻለኝም፡፡

ህወሃት ለሚናፍቀው ጄኖሳይድ መፈፀም በትክክል የሚያገለግሉ ግብአቶችን ህወሃት ከበቂ በላይ ያከማቸለን ከመሆኑ የተነሳ እንደ ህዝብና እንደ ሀገር ይህንን ሴራውን ሊያስከሽፍ በሚያስችል አካሄድ ካልሄድን የመፈፀሙን አይቀሬነት ስናገር ጄኖሳይድ ናፋቂ ሆኜ አይደለም፡፡

አካሄዳችንን ካልቀየርን፤ በተለይም የትግራይ ህዝብ አሁን እራሱን ካስገዛበት የህወሃት እስር ካላስለቀቀና በመያዣነቱ በዝምታ ድባብ ተጀቡዶ ዝም ካለ የህወሃት ጄኖሳይድ ድግስ በገፍ ቀርቦ መፈትፈቱ አይቀሬ ነው፡፡

***

***የጄኖሳይድ ምስጢራዊ ጥቅም ለህወሃት-

የወልዲያው ግጭት በተለየ ሁኔታ በነገድ ላይ ያነጣጠረ ጄኖሳይድ ነው የሚለው የህወሃታዊያን መንደር ጩህት ከመሬት ተነስቶ አይደለም ስርዓቱ እንዲስተጋባ እያደረገ ያለው፡፡

የንግድ ተቋሞቹና የድርጅቱ ንብረቶች በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍል ኢ-ላማ እየተደረጉበት ከመውደማቸውም በላይ በአማራና በኦሮሚያ የተከሰተውን የትብብርና የአንድነት መንፈስ ወደ ትግራይ ደጃፍ በምንም አይነት መንገድ እንዲቀርብና ብሎም እንዲያንኳኳ ከቶም አይፈልግም፡፡ ዛሬ ህወሃት ላለፉት 26ዓመታት የተሞረኮዘበትን ኢህአዴግ ምርኩዝ እንክትክቱ በወጣበት ወቅት ድርጅቱ የስልጣኔና የህልውናዬ ምንጭና የጀርባ አጥንት የሚለውን የትግራይን ህዝብ ድጋፍና ሙሉ በሙሉ ተገዢ ታዛዥነት ማጣት ማለት የእስትንፋሱ ህቅታ ማለት እንደሆነ ቀድሞ የተለመው እውነታ ነው፡፡

የወልዲያው ጄኖሳይድ ጩህት ዋና ምስጢር በአንድ ድንጋይ ሁለት ወፍ እንዲሉ ህወሃት በጄኖሳይዱ ጩህትና ክስ -

1ኛ-በሀገሪቱ ውስጥ እየተፈፀመ ያለውን የህወሃትን ንብረት የማውደምን እርምጃ ለመከላከያነት

2ኛ-ከተቀረው የኢትዮጵያ ክፍል የቀረበበትን እና ለስልጣኑ አስጊ የሆነውን ህዝባዊ አመጽ መሸሸጊያ፣መመከቺያና ብሎም ማምለጫ ምሽግ ብሎ የሚጠራውን የትግራይን ክልል ከተቀረው ህዝብ ጋር ያለውን የሰለለ ግንኙነት መስመር በመዝጋት ህዝቡን ሙሉ በሙሉ የፍላጎቱ ተገዢና ፈጻሚ ለማድረግ ሲል የወልዲያውን ክስተት ከዘር ተኮር ጥቃት ጋር በማያያዝ ጄኖሳይድን ሲያስተጋባ እያየን ነው፡፡

ለምንድነው የትግራይ ህዝብ መገንጠል አለበት የሚል ይፋዊ ክርክር የከፈተው፤? በወልዲያ በትግራይ ህዝብ ላይ በተፈጸመው ጄኖሳይዳዊ ጭፍጨፋ ምክንያት ነውን? ይህ ቀደም ብሎ ታስቦበትና ፕላን ወጥቶለት የነበረን እቅድ ምንም ያልተፈፀመን ጄኖሳይድ በወልዲያ ተፈፀመ በሚል ወዲያው ይፋ ማድረጉ የድርጅቱን በጄኖሳይድ ምስጢራዊ ተጠቃሚነትን በጥቂቱ ገላጭ ነው፡፡

ምንግዜም ዘር ተኮር ቁፍጨፋ እሚፈጸመው ስልጣንና ሃይልን በተቆጣጠረው ገዢ ክፍል እንጂ ተጨቋኝ ሆኖ እሱ እራሱ ነጋ ጠባ እየተሳደደና እየተጨፈጨፈ ባለ ነገድም ይሁን ህዝብ አይደለም፤ ሆኖምም አያውቅም፡፡

በርካታ የትግራይ ተወላጅ ያልሆኑ ኢትዮጵያዊያን በሰው ልጅ መብት መከበርና እኩልነት በማመን ማንም ይሁን ማን በማንነቱ ምክንያት መጠቃትን እናወግዛለን የሚል ድንቅ አቋም ሲያንጸባርቁ ማስተዋል የተቻለ ቢሆንም በትግራይ በኩል ግን አጠቃላይ የትግራይ ተወላጅ የሆነ ሁሉ የህወሃት አባልና ደጋፊ ሆነ አልሆነ በትግራዋይነቱ መነካት የለበትም የሚል ግለ-ፍላጎትን ብቻ መሰረት ያደረገ አቋም ሲያንፀባርቁ ለማየት ተችሏል፡፡

መልካም የትግራይ ተወላጅ በማንነቱ መነካት የለበትም የሚለውን አባባላቸውን ባልቃወምም ምሉእነት የሚኖረው ግን አማራውም፣ኦሮሞውም፣ጋምቤላውም....ወዘተ ሁሉም በተፈጥሮአዊ ማንነቱ መጠቃት የለበትም ቢሉ እውነተኛ የሆነ የሰው ልጅ አቋም እንዳንፀባረቁ ይሰማኝ ነበር፡፡

ከትግራይ ህዝብ ብዙ ይጠበቃል- ቀሪው የኢትዮጵያ ህዝብ በውል ባልተረጋገጠው የወልዲያ ግጭት ላይ የትግራይ ተወላጆች በማንነታቸው የደረሰባቸውን ጥቃት እናወግዛለን ሲል አጋርነቱን ቢያሳይም ከትግራይ ተወላጆች በኦሮሚያ፤በአማራ፤በጋምቤላ፤በኮንሶና በአፋር ዜጎች በማንነታቸው ሲጠቁ ያሰማው ድምጽ ስለመኖሩ የማውቀው ነገር የለም፡፡ ከእነድነ አቶ አብርሃም ያዬ፤አቶ ግደይ ዘራጺዮን እና መሰል ትቂቶች በሰተቀር፡፡

አቶ አብርሃም ያዬ ከሆላንድ ለትግራይ ወገናቸው በላኩት መልእክት ጽሁፌን ልደምድም«አንተ የትግራይ ህዝብ በወልዲያ፤ጎንደር፤ኦሮሚያና ደቡብ እየኖረክ ሀብትና ጥሪት አፍርተህ እንዴት ሆኖ ነው ለትልማ የምታዋጣው?» ካሉ በሃላ አክለውም «ባለህበት፤በምትኖርበትና ሀብት ባፈራህበት አዋጣ እንጂ ለትልማ አታዋጣ፤ወገኖችህ ሲገደሉ እሪ፤እሪ እያልክ ጩህ እንጂ ዝም እንዳትል» ሲሉ መክረዋል፡፡
ቸር እንሰንብ--

------------
ኢ-ሜይል ኢትዮሚዲያ ወይም በግሌ teklu7@gmail.com ጻፉልኝ እመልሳለሁ፡